## የጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰበር የመጨረሻ ውሳኔዎችን መስማት ፣ ከተከራካሪ ወገኖች ለአንደኛው የተሰጠ ሌላ የይግባኝ መብት ?

የሴና ገ/እግዚአብሔር *

የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ጠቅላይ ፍ/ቤት ካሉት የግዛት ሥልጣናት መካከል አንዱ ፡

በጠቅላይ ፍ/ቤት ወይም በሌሎች ፍ/ቤቶች የተሰጠ የመጨረሻ ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ሲገኝ ወይም በሥነ ሥርዓት ሕጎች ውስጥ በተመለከቱት ሌሎች ምክንያቶች በሰበር መስማት ይገኝበታል ።[1]

ጠቅላይ ፍ/ቤት ይህንን ተግባር ያከናውን ዘንድ ሕጉ የሚከተለውን ይደነግጋል ።

በጠቅላይ ፍ/ቤት ወይም በሌላ በማናቸውም ፍ/ቤት የተሰጠ የመጨረሻ ውሳኔ በሰበር የሚሰማው በጠቅላይ ፍ/ቤት ፡ በፕሬዚዳንቱ ወይም በምክትል ፕሬዚዳንቶቹ በአንዱ ሰብሳቢነት [2] በተጨማሪ ቢያንስ አራት የጠቅላይ ፍ/ቤት ዳኞች በሚሰየሙበት ችሎት [3] ይሆናል ።

ጉዳዮች በሰበር ይሰሙ ዘንድ የማንቀሳቀስን ሥልጣንና ኃላፊነትን በተመለከተም የሚከተለውን ተመልክተናል ።

> በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 4 መሠረት የመጨረሻ ውሳኔ በሰበር የሚሰማው የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ሲፈቅድ ወይም ጠቅላይ ዐቃቤ ሕጉ ተቃውሞ ሲያቀርብ ነው ። [4]
>
> እነዚህን ድንጋጌዎችም ሲመረመሩ የሚከተለውን ጭብጥ ያስነሳል ። በጠቅላይ ዐቃቤ ሕጉ ወይም በጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ምርመራ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ስለመሆኑ የተገኘ የመጨረሻ ውሳኔ እኳያ የባለጉዳዮቹ ሚና ምንድን ነው ?

በልዩ ሁኔታ ሲቀመጥ ፣ ይህ አጠቃላይ ጭብጥ ወደሚከተሉት ጭብጦች ሊከፈል ይቻላል ።

/1/ ይህ ሰሚ እንደማንኛውም ተራ ይግባኝ ጠቅላይ ፍ/ቤት ባለጉዳዮችን እንደ ይግባኝ ባይና መልስ ሰጭን የሚጠራበት ሌላ ይግባኝ ነውን ?
/2/ ከሆነስ ፡ ሰሚው እንደማንኛውም ሌላ ይግባኝ በባለጉዳዮቹ ፍላጐት ላይ ይመሠረት ይሆን ?

ከላይ በ/1/ ና በ/2/ ላይ ለተጠቀሱት ጭብጦች የምንሰጠው መልስ አፍራሽ ከሆነ ፡

/ሀ/ በሰበር ሰሚው የተሰጠውን የመጨረሻ ውሳኔ በተመለከተ ባለ ጉዳዮቹ ምንም የሚጫወቱት ሚና የለም ማለት ይሆን ?

/ለ/ ከሆነስ በሰበር ሰሚው በሚሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ ላይ በባለጉዳይነት የሚወርሱት እነማን ይሆናሉ ?

የሰበር ሰሚው በመጨረሻ ውሳኔዎች ላይ የሚያደርገው ምርመራ በወንጀልነክ ጉዳዮች ብቻ ያልተወሰነ መሆኑን ስንመለከት የባለጉዳዎችን ሚና በተመለ

ኩት ያነሰ ነው ። ጭብጥ ከምንጊዜም የበለጠ ተገቢ ሆኖ እናገኘዋለን ። የፍትሐብ ብሔር ጉዳዮችን በተመለከተም ጭምር የሚቻል ሆኖ ይገኛል ። የወንጀል ነክ ጉዳ ዮችን በተመለከተ አወሳሰናቸው በጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ መሥሪያ ቤት [5] የማዘዝ ሥልጣን ሥር መሆኑ ግልጽ ነው ። ስለሆነም የወንጀል ነክ ጉዳዮችን በተመለከተ የሚቀርበው የመጨረሻ ውሳኔ ሰሚ አብዛኛውን ጊዜ በጠቅላይ ዐቃቤ ሕጉ የተቃ ውሞ አቤቱታ መሆኑን መገመት ተገቢ ሆኖ ይገኛል ። በዐቃቤ ሕግ መሥሪያ ቤት [6] ተግባራት መካከል አንዱ የግለሰቦችን አካላዊም ሆነ ሕጋዊ መብቶች መከበራ ቸውን ማረጋገጥ መሆኑን ስንመለከት ከላይ የጠቀስነው አስተያየት ከምን ጊዜ ውም የበለጠ ተጨባጭና እሙን ይሆናል ። ስለዚህ በወንጀል ነክ ጉዳዮች ላይ " መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት በተገኘ ጊዜ የመጨረሻው ውሳኔ በሰበር ይሰ ሙ ዘንድ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ የተቃውሞ አቤቱታ እንዲሰማ ዐቃቤ ሕጉ ያሳስ ባል ። " በዚህም ዐቃቤ ሕጉ እንደ አንደኛው ተከራካሪ ወገን ሊወሰድ ይቻላል ። የተደረገው መሠረታዊ የሕግ ስህተት የሚጐዳው የተከሰሰውን ተከላካይ ወገን ፍላጐት ቢሆንም እንኳን ዐቃቤ ሕጉ እንደ ዕለት ከዕለት ሥራው በመቁጠር አቤ ቱታውን እንዲያሰማ ይጠበቅበታል ። በፍትሐ ብሔር ጉዳዮች ላይ ግን ይህንን ጉዳይ ለመፈጸም የሚችል የመንግሥት አካል የሆነ መሥሪያ ቤት በባለጉዳይነት አይቀርብም ። ስለዚህ " መሠረታዊ የሕግ ስህተት " ያለበትን ፍትሐብሔር ነክ የመጨረሻ ውሳኔ አንዱ ወገን ለጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ወይም ለጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬ ዚዳንቱ እስካላሳወቀ ድረስ የተሰጠው ውሳኔ ሕጋዊ እንደሆነ ሊቆይ ይችላል ። ከእ ነኝህ ባለሥልጣናት መካከል አንዳቸው በሆነ መንገድ የሕግ ስህተት ያለበት ፍት ሐብሔር ነክ የመጨረሻ ውሳኔ የተሰጠ መሆኑን ሊደርሱበትም ይችላሉ ። ከዚህ በላይ ከጠቀስናቸው አኳኋኖች ውጭ " መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያላቸው " ፍት ሐብሔር ነክ የመጨረሻ ውሳኔዎች ከሕግ ውጭ ቢሆኑም እንኳን በሥራ ላይ ከመ ዋል የሚያግዳቸው ነገር አይኖርም ። ይህን የመሳሰሉ የመጨረሻ ውሳኔዎችን ወደ ሚመለከተው ባለሥልጣን ፊት ሊያቀርብ የሚችል መንግሥታዊ መዋቅር እስከ ሌለ ድረስ ከላይ የጠቀስነው ጉዳይ ሐቅ ይሆናል ።

ፍትሐብሔር የተበዳይ ወገኖች የግል ጉዳይ እንደመሆኑ መጠን " መሠረ ታዊ የሆነ የሕግ ስህተት " ያለበት የመጨረሻ የፍትሐብሔር ውሳኔ ለምን እነዚ ህን ታላላቅ የመንግሥት ባለሥልጣናት ይጠቅሳቸዋል ? የሚል ተገቢ ጥያቄ ሊቀ ርብ ይችላል ። ነገር ግን የመጨረሻ ውሳኔዎችን በሰበር ስለመስማት ከላይ የተጠ ቀሱት የሕግ አንቀጾች የፍትሐብሔርንም ጉዳይ የሚጨምሩ ሆነው እናገኛቸዋ ለን ።

በተጨማሪ በጠቅላይ ፍ/ቤት ልዩ ችሎት አንድ ጉዳይ በሰበር እንዲሰማ ማመ ልከቻ ሊቀርብ የሚችልበትን ጊዜ ማስተዋልም እጅግ ጠቃሚ ነው ። ይኸውም የሚሆነው ፦—

> . . . ውሳኔ በተሰጠ በ6 ወራት ውስጥ ይሆናል ። ሆኖም የተለያዩ ምክ ንያቶች ካጋጠሙና ጥያቄው በወንጀል የእሥራት ቅጣት የተፈረደበ ትን ተከሳሽ የሚጠቅም ሆኖ ሲገኝ ፍርድ ቤቱ ከላይ በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ላይወሰን ይችላል [7]።

ከላይ እንደተጠቀሰው " መሠረታዊ የሕግ ስህተት " ያለበት ፍትሐብሔር ነክ የመጨረሻ ውሳኔ በሰበር ታይቶ ውሳኔ ይሰጥበት ዘንድ ለሕጉ ሊያቀርበው የሚችል መዋቅር አለመኖሩ ሁኔታውን ማወቅ በአብዛኛው ለአስተሳሰብና ትም ህርታዊ እንዲሆን አድርጎታል ። የግል ባለጉዳዮችም ቢሆኑ " መሠረታዊ የሕግ

ስህተት ” በሚታይበት ጊዜ ምቹ በሆነ ዘዴ ሕግ ፊት ሊያቀርቡት አለመቻላ
ቸውን ተገንዝበው ከወዲሁ ተስፋ ስለሚቆርጡ ከነጭራሹ አይጨነቁበትም ።
ጉዳዩ የሚመለከታቸው የመንግሥት ባለሥልጣናትም ቢሆኑ በውሳኔ ላይ የታየው
“ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ” ቢስተካከል የግል ባለጉዳዮችም የሚጠቀሙበት
ሆኖ ካላገኙት እንዲያው ኃላፊነት ብቻ ተሰምቷቸው ጉዳዩ በሰበር እንዲታዩ አያ
ደርጉም ። ነገር ግን ይህ አመለካከት የግል ባለጉዳዮች በመጨረሻ ውሳኔዎች “መ
ሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ” በሚኖርበት ጊዜ ጉዳዩን በሰበር ይሰማ ዘንድ
ሊጫወቱት የሚገባውን ሚና በተመለከተ ሙሉ መፍትሔ ሊሰጠን አይችልም ።

የጠቅላይ ፍ/ቤትም ቢሆንም ይህንን ልዩ የሆነ ውሳኔዎችን የመከለስ ሥል
ጣን ለምን እንደተሰጠው ፣ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ መሥሪያ ቤትም ሆነ የጠቅላይ ፍ/
ቤት ፕሬዚዳንት ጉዳዮችን ለማንቀሳቀስ ይህ ኃላፊነት ለምን እንደተሰጣቸው ለመ
ረዳት ከላይ በዝርዝር የተመለከትነው ሁኔታ ሊያስረዳን አይችልም ።

ስለሆነም ጠቅላይ ፍ/ቤቱም ሆነ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ መሥሪያ ቤት ወይም
ሁለቱም የመንግሥት አካላት በተሰጣቸው ሥልጣንና ኃላፊነት ከተቋቋመበትም
ዓላማ አንጻር ሲታይ “ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ” ያለባቸውን የመጨረሻ
ወንጀል ወይም ፍትሐብሔር ነክ ውሳኔዎችን ወደ ሕግ ፊት አቅርበው እንዲስተ
ተካከሉ ባያደርጉ የተሰጣቸውን ኃላፊነትና ሥልጣን ያልተወጡ እንዲሁም የተ
ቋቋመበትን ዓላማ ዘንግተዋል ሊያሰኛቸው የሚችል ነገር ቢኖር መመርመሩ አስ
ፈላጊ ይሆናል ። ሁብቱም መሥሪያ ቤቶች “ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ” ያለባቸ
ውን ወንጀልም ሆነ ፍትሐብሔር ነክ የመጨረሻ ውሳኔዎች በሰበር ታይተው እን
ዲስተካከሉ ማድረግን በግድ የሚጠይቁ ሌሎች ዓላማዎችና ተግባራት ሊኖሩዋ
ቸው ይችሉ ይሆናል ። የመጨረሻ ውሳኔዎች በሰበር መስተካከል ሊኖሩት ከሚች
ሉት ዓላማዎች መካከል ፍ/ቤቶች ከስህተታቸው ይታረሙ ዘንድ የሚሰጠው ጥ
ቅም ለማንም የተሰወረ አይደለም ። ነገር ግን ይኸን የመሰለ ዓላማ እንኳን በማይ
ኖርበት ጊዜ የመጨረሻ ውሳኔዎችን በሰበር የማሰማት ጥያቄ ዐቃቤ ሕግ በባለጉዳ
ይነት በማይወክልበት ጊዜ ሙሉ በሙሉ የመጨረሻው ውሳኔ የሚመለከታቸው
ባለጉዳዮች ምርጫ ይሆናል ከማለት በስተቀር ሌላ አማራጭ አይኖረንም ። ስለ
ሆነም እስቲ ከላይ የጠቅስነው ዓላማ ፣ ሥልጣንና ኃላፊነት ለነዚህ መንግሥታዊ
አካላት ተሰጥቶ እንደሆነ ለማረጋገጥ እነኝሁ አካላት የተቋቋመበትን ዓላማ ፣ ያላ
ቸውንም ሥልጣንና የተግባር ኃላፊነት እንመልከት ።

የዐቃቤ ሕግ መሥሪያ ቤት ካሉት ሌሎች ዓላማዎች በተጨማሪ የሚከተሉ
ትም ይኖሩታል ፡—

> የኢትዮጵያ ዲሞክራቲክ ሪፑብሊክ ሕጎች ደንቦች ትዕዛዞችና መመ
> ሪያዎች ሳይዛቡና በሁሉም ቦታ በአንድ ዓይነት ተፈጻሚ መሆናቸውን
> ማረጋገጥ ፤ [8] በሕገ መንግሥቱና በሌሎች ሕጎች የተረጋገጠ የዜጎች
> መብቶችና ነጻነቶች እንዲከበሩ ማድረግ ።

ሥልጣንና ተግባርን በተመለከተ የጠቅላይ የዐቃቤ ሕግ መሥሪያ ቤት ደግሞ
ከሌሎች በተጨማሪ የሚከተለው ሥልጣንና ተግባር ተሰጥቶታል ።

> ሕግ መንግሥቱና ሌሎች ሕጎች ደንቦችና መመሪያዎች በሚኒስቴሮች
> የመስተዳደሩ አካል በሆኑ ሌሎች መሥሪያ ቤቶች በማምረቻ በማከፋፈ
> ያና በአገልግሎት ሰጪ ተቋሞች በሕዝባዊ ድርጅቶች በሕብረት ሥራ
> ማህበራት በአካባቢዎች ውስጥ በሚገኙ አስፈጻሚ አካላት በባለሥል

> ልጣኖቻቸውና በማንኛውም ግለሰብ መከበራቸውንና በትክክል ሥራ ላይ መዋላቸውን በመቆጣጠር ሶሻሊስት ሕጋዊነትን ማረጋገጥ ። [9]

በሌላ ወገን የጠቅላይ ፍርድ ቤትም ፡ ካሉት ሌሎች ዓላማዎች በተጨማሪ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል ።

> በሕግ የተጠበቁትን የግለሰቦች መብቶች ጥቅሞችና ነጻነቶች ማስከበር፤ የሕግና የሥርዓት መጠበቅ እንዲጠናከር ሶሻሊስት ሕጋዊነት እንዲከበር ማድረግ ። [10]

ሥልጣንና ተግባርን በተመለከተ ደግሞ የጠቅላይ ፍ/ቤት ከሌሎች በተጨማሪ የሚከተለው ሥልጣንና ተግባር አለው ፡—

> የዳኝነት አሠራርን ለማሻሻል የሕጐችን አንድ ወጥ አፈጻጸም ለማረጋገጥ ለፍ/ቤቶች መመሪያ መስጠት ። [11]

ከዚህ በላይ የጠቀስናቸው በሙሉ የጠቅላይ ፍ/ቤትም ሆነ የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ መሥሪያ ቤት የሕጐችን በትክክልና አንድ ወጥ አፈጻጸም የማረጋገጥ ሥልጣንና ተግባራት አሉዋቸው ።

በኢትዮጵያ ውስጥ በማንኛውም ሥፍራ ማንኛውም የመንግሥት አካል ፣ በተለይም ፍ/ቤቶች ፣ ሕዝባውያን ድርጅቶች ፡ አምራች ፡ አከፋፋይና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶችና እንዲሁም ሌሎች በአገሪቱ ውስጥ የሚገኙ ተቋሞች በተለይም ለአሠራራቸው ተገቢና ተግባራቸውንም ለመወጣት የሚጠቅሟቸውን ሕጐች በትክክልና በአንድ ወጥነት ሥራ ላይ መዋላቸውን የማረጋገጥ ኃላፊነትና ግዴታ ተጥሎባቸዋል ።

በሌላ አነጋገር አንድ ወጥ የሆነ የሕግ አጠቃቀም እንዲኖር ማናቸውም መንግሥታዊ ተቋሞች ፡ ሕዝባውያን ድርጅቶችና ሌሎችም የመንግሥት አካላት ሥልጣናቸውንና ተግባራቸውን ሕጋዊ በሆነ መንገድ ማከናወን አለባቸው ። ይህም ማለት በአንድ ዓይነት ውሳኔ ሥር የሚገዙ ሁኔታዎች ውሳኔውን የሰጠው ግለሰብ ማንም ይሁን ማን ወይም የተሰጠው ውሳኔ የሚመለከተው ወይም ሊነካው የሚችለው ግለሰብ ማንም ይሁን ማን ፣ በአንድ ዓይነት መንገድ መታየት ይኖርበታል ። የሕጉ ትክክለኛና አንድ ወጥ አጠቃቀም የተንጸባረቀባቸው ውሳኔዎች ከሌሎች በተጨማሪ የሚከተሉትን ያካተቱ መሆን አለባቸው ፡—

ሀ/ ንግድ ለማካሄድ የሚያስፈልገውን ፈቃድ ለመስጠት የሚደረጉ አስተዳደራዊ ውሳኔዎች በግለሰቦች ሊካሄዱ የሚችሉትን የንግድ ዘርፎች ከሌሎች መለየት ፣ ለተመሳሳይ የሥራ መስኮች ሊከፈሉ የሚገባቸውን የደመወዝ መጠን መወሰንና የመሳሰሉትንና ፣ እና ፤

ለ/ በደል የደረሰባቸው ግለሰቦች የሚካሱበትን ዘዴ ለመሻት የሚደረጉ ሕጋዊ ውሳኔዎች ፣ በደል አድርሰው የተወነጀሉ ግለሰቦችን በጥፋተኛነት መያዝ ፣ በተያዙበት ወንጀል ጥፋተኛነታቸው የተረጋገጠባቸው ወንጀለኞች ላጠፉት ጥፋት ተገቢ የሆነ ቅጣት የሚያገኙበትን ሁኔታ መሻትና የመሳሰሉትን ።

ፍ/ቤቶች የመጨረሻ ውሳኔ ላይ ለመድረስ ችሎት ማስቻላቸው ግልጽና የታወቀ ጉዳይ ነው ። የወንጀልም ሆነ የፍትሐብሔር ችሎቶችን ለማስቻልና እነኝህም ሁኔታዎች የሚገዙበት ሕጐች መኖራቸው ደግሞ በእንጻሩ ግልጽ ሆኖ ይገኛል ። ስለዚህም ፍርድ ቤቶች የወንጀልም ሆነ የፍትሐብ

ሔር ጉዳዮችን በሚመለከቱበት ጊዜያት በሙሉ ጠቅላላው ሕጋዊ ሂደት በተ
ገቢ ሕጎች ትክክልና አንድ ወጥ አጠቃቀም ላይ የተመረኮዘ መሆን አለበት ።
ባለጉዳዮችም ቢሆኑ ፍርድ ቤቶች የመጨረሻ ውሳኔ ለመስጠት አንድ ወጥና ትክ
ክለኛ ሕግ በሥራ ላይ ማዋላቸውንና መጠቀማቸውን ማየት የዘወትር አትኩሮታ
ቸው ሆኖ ይገኛል ። የፍርድ ቤቶች የመጨረሻ ውሳኔዎች አንድ ወጥና ትክክለኛ
በሆኑ ሕጎች ላይ እስከተመሠረቱ ድረስ ፣ ችሎቶች የተካሄዱት ትክክለኛና አንድ
ወጥ ሕጋዊ መንገድን ተከትለው ይሁን ወይም አይሁን በአብዛኛው የባለጉዳዮች
ችግር (ጭንቀት) ሆኖ አይታይም ። አንድ ወጥና ትክክለኛ የሆነ የሕግ አጠቃቀም
ካለና ይህም በሥራ ላይ መዋሉ በመንግሥት አካላት የቅርብ ክትትል የሚደረግ
በት እስከሆነ ድረስ የወንጀልና ፍትሐብሔር ነክ ጉዳዮች በችሎት በሚታይበት
ጊዜ ፍርድ ቤቶች ትክክለኛና አንድ ወጥ ሕግ መጠቀም ይኖርባቸዋል መባሉ ያል
ተለመደ ጉዳይ ነው ሊባል አይቻልም ። ከዚህ በላይ የጠቀስነው ጉዳይ የጠቅላይ
ፍ/ቤት በችሎት በተሰየመበት ጊዜ ሁሉ በግብርና ሊተረጉመው የሚገባ ጉዳይ
በላይ የተቋቋመበት ስላማዊ ሆኖ ይገኛል ። በሌላ አነጋገር ፍ/ቤቶች ችሎት በሚ
ያስችሉበት ወቅት ሕጎችን በትክክልና በአንድ ወጥነት መጠቀማቸውን ማረጋ
ገጥ የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ መሥሪያ ቤት ኃላፊነት ብቻ አለመሆኑን እንገነዘባለን ።
ከጠቅላይ ፍ/ቤት ተግባራት መካከልም እንደ አንዱ ሆኖ ተቀምጧል ።

ከላይ ከተጠቀሱት የዐቃቤ ሕግ ተግባራትና ሥልጣናት እንደምንገነዘበው
ሶሻሊስት ሕጋዊነት ማለት ጉዳዩ የሚመለከታቸው ባለሥልጣናት በሙሉ አንድ
ወጥና ትክክለኛ የሆነ ሕግ በመላው አገሪቱ ጥቅም ላይ መዋሉን ከማረካገጥ ሌላ
ምንም ነገር ሊሆን አይችልም ። ይህ ኃላፊነት ደግሞ በኅብረተሰቡ ውስጥ በተራ
ባለጉዳይነትም ሆነ ውሳኔዎችን ለመስጠት ሥልጣን ያላቸውን የመንግሥት ባለ
ሥልጣናትም የሕግን በደንብ በሥራ ላይ መዋል ማረጋገጥን ጭምር ሊሆን ይች
ላል ።

ሶሻሊስት ሕጋዊነትን ዘንድ (በግብር ይታይ ዘንድ) የሕጎችን አንድ ወጥነ
ትና ትክክለኛነት ማረጋገጥ ከላይ የጠቀስናቸው ሁለቱ የመንግሥት አካላት ተግ
ባራትና ሥልጣናት መሆናቸው የሆነው ሆኖ አንድ መንግሥታዊ መሥሪያ ቤት
ሥራውን ያከናውን ዘንድ አንድ ወጥና ትክክለኛ የሕግ አጠቃቀምንም ማረጋገጥ
በተመለከተ የጠቅላይ ፍ/ቤት የቁጥጥር ሥልጣን በፍ/ ቤቶች አካባቢ ብቻ የተወ
ሰነ ነው ። በሌላ ወገን ደግሞ የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ በማናቸውም የመንግሥት አካ
ላት [12] ውስጥ አንድ ወጥና ትክክለኛ የሕግ አተረጓጎምና አጠቃቀም የማረጋገጥ
ኃላፊነት ቢኖረውም ይህ ኃላፊነት የፍርድ ቤቶችን ሕጋዊ እንቅስቃሴዎችን አይ
ጨምርም ። በተጨማሪ ግን የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ መሥሪያ ቤት ወይም የጠቅላይ
ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት በሚሰጠው ውሳኔ መሠረት የጠቅላይ ፍርድ ቤት የሕጎ
ችን አንድ ወጥና ትክክለኛ አጠቃቀም የማረጋገጥ ተግባር ያከናውናል ። ነገር ግን
በሥልጣን ዝቅተኛ የሆኑ ፍርድ ቤቶች ሥራቸውን ሲያከናውኑ ሕጎ
ችን በአንድ ወጥነትና በትክክለኛነት በሥራ ላይ መዋላቸውን መቆጣጠር የጠቅ
ላይ ፍርድ ቤት አንዱ በሕግ አውጭው የተሰጠው ሥልጣኑ መሆኑ አይካድም ።
በተሰጠው ውሳኔ አንዱ ወገን ይግባኝ ቢልም ከላይ የጠቀስነው የጠቅላይ ፍርድ
ቤት ተግባርና ኃላፊነት በማናቸውም ጊዜ መከናወን ይገባዋል ። ባለጉዳዮች በመ
ሠረቱ ይግባኝ የሚያቀርቡት የመጨረሻ ውሳኔን በተመለከተ ብቻ ስለሆነ ጠቅ
ላይ ፍርድ ቤት በማናቸውም ጊዜ በራሱ አነሳሽነት ከላይ የጠቀስነውን ቁጥጥር
ማድረግ የሚገባው መሆኑን የበለጠ ያጠናክርልናል ። የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ መሥ
ሪያ ቤት አቤቱታም ሆነ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት የሚሰጠው ውሳኔም ቢ

ሆን ሁለቱም ሊንቀሳቀሱ የሚችሉት የጠቅላይ ፍርድ ቤት ንም ሆነ የሌሎች አነስተኛ ፍርድ ቤቶች የመጨረሻ ውሳኔን ብቻ ተመርኩዘው ነው ።

የጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉዳዮችን በሰበር በሚመለከትበት ጊዜ ፕሬዚዳንቱ ወይም ምክትል ፕሬዚዳንቶች በአባልነት እንደሚገኙ የተገለጠ መሆኑ ጉዳዩን የሚመለከተው ጉባኤ [13] ከላይም የጠቀስነውን ተግባሩን ይወጣ ዘንድም ይረዳዋል ። ይሁን እንጂ የሕጎችን አንድወጥ አጠቃቀም በበላይነት የመቆጣጠርና የመመልከት ተግባር የጠቅላይ ፍርድ ቤት ተግባራት በአጭሩ ሲታዩ የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ጽ/ቤት ነው ማለትም ይቻላል ። በሌላ ወገን ደግሞ “ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ” ያለባቸውን የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በዐቃቤ ህግ ወይም ፍትሐብሔር ነክ ጉዳይ ሲሆን ከተከራካሪዎቹ በአንዱ አማካይነት ሲቀርብለት በመመልከትና ሶሻሊስት ሕጋዊነትንም ማረጋገጥ ሆነው ይገኛሉ ። የመጨረሻ ውሳኔዎችን በሰበር ስለሚመለከትን ስናጤን (የአንድ ውሳኔ መሻር ስሜት ሊሰጥ የሚችለው በሚደረገው መሻር ቢያንስ አንዱ ወገን የሚጠቀምበት ሆኖ ሲገኝ ነው ከሚለው እውነታ አንጻር ሲታይ) ተበደልኩ ባይ አንዱ ወገን ጥያቄውን በአቤቱታ ወይም በማመልከቻ መልክ እንዲሰማ ካላቀረበው በቀር የጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉባኤ የመጨረሻ ውሳኔዎችን በሰበር የመስማት ተግባር አይኖረውም ።

የሆነው ሆኖ “ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ” ያለባቸውን የመጨረሻ ውሳኔዎችን ለማሻሻል ረገድም ቢሆን ውሳኔው ይመረመርለት ዘንድ የሚፈልግ ወገን ማድረግ የሚችለው ለጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉባኤ የሶሻሊስት ሕጋዊነትን ስሜት በተመረኮዘ ሁኔታ አቤት ማለት ይሆናል ። ይህም ፍርድ ቤቶች የመጨረሻ ውሳኔያቸውን በሚሰጡበት ጊዜ ሶሻሊስት ሕጋዊነትን መመሪያቸው ያደርጉ ዘንድ አንዱ አረጋጋጭ ሁኔታ ሆኖ ይገኛል ። ከላይ የጠቀስነው ሁኔታ መደበኛ ይግባኝ በተመለከተም ጭምር እውነታ አለው ። ስለዚህ ፣ የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ መሥሪያ ቤት ማንም ተከራካሪ ወገን እንደሚያደርገው ሁሉ በራሱ አነሳሽነት የሶሺያሊስት ሕጋዊነትን በተግባር መተርጐምና በሥራ ላይም መዋልንም ጭምር አስገዳጅነት ሊጠይቅ አይችልም ። አይገባውም ! በሌላ በኩል ግን ፣ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ጉባኤ እንደማናቸውም መደበኛ ፍርድ ቤት የማናቸውንም መደበኛ ፍ/ቤቶች የጠቅላይ ፍ/ቤትን ጨምሮ የመጨረሻ ውሳኔዎችን በሌላ ተለዋጭ ውሳኔ መተካትና የውሳኔውንም አፈጻጸም በአስገዳጅነት የመጠየቅ መብትና ሥልጣን ተሰጥቶታል ። ይህንን ካልን ዘንድ የጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ሰሚ ጉባኤ የፍርድ ቤቶችን የመጨረሻ ውሳኔዎች በተመለከተ የወንጀል ጉዳዮችንም ቢሆን ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ቢቃወምም እንኳን “ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ” አለባቸው ብሎ የሚገምታቸውን የመጨረሻ ውሳኔዎች በሙሉ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት በሚሰጠው ውሳኔ መሠረት ለመሰረዝና በሌላ ተለዋጭ ውሳኔ ለተመለከተ ተግባርና ኃላፊነት ተሰጥቶታል ማለት እንችላለን ። የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግም ሆነ ሁለቱ ተከራካሪ ወገኖች በአንድ የመጨረሻ ውሳኔ ውስጥ “ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት” ኖረውም አልኖረውም የሚኖራቸው አቋም በክለሣ ሲታይ ለሚሰጠው ውሳኔ ምንም ፋይዳ አይኖረውም ። ነገር ግን ውሳኔውን ማሻሻል ለሚችለው ጉባኤ እንደተጨማሪ አሳማኝ ሁኔታ ሆኖ መቅረቡ አያጠራጥርም ።

የጠቅላይ ፍርድ ቤት ማናቸውንም የመጨረሻ ውሳኔ በሰበር በሚያይበት ጊዜ በበታች ፍ/ቤቶች ዘንድ የሕጐችን አንድ ወጥ አሠራር የማረጋገጥ ተግባሩን እየተወጣ መሆኑ አያጠራጥርም ። ምክንያቱም ውሳኔዎችን በሰበር መመልከት ልክ እንደማንኛው ተራ ይግባኝ ከላይ የጠቀስነውን የጠቅላይ ፍርድ ቤት ተግባር በግልጽ ስለሚያመለክት ነው ። ይህንን ካልን ዘንድ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ

ጉባኤ ከተከራካሪ ወገኖች ፍላጐትና ግምት ውጭ እንኳን ቢሆን በሰበር ውሳኔዎችን በመለወጥና በማሻሻል የሕጎችን አንድ ወጥ አጠቃቀም በማረጋገጥ ረገድ የመልካም ሕግና ፍትህ አስተዳደር የሚሰፈን ኃላፊነቱን ይወጣል ። በአንጻሩ ደግሞ ወንጀል ነክም ሆነ ፍትሐብሔር ነክ የመጨረሻ ውሳኔዎችን በጠቅላይ ፍ/ቤት ጉባኤ ከሰበር መስማት ለተከራካሪ ወገኖች እንደ ተሰጠ እንደ አንድ ተጨማሪ የይግባኝ መብት መቁጠር በፍጹም ስህተት መሆኑ ሊጠቀስ ይገባል ።

ነገር ግን " የሕጎች አንድ ወጥ አጠቃቀም " ለማረጋገጥ ብቻ ሲባል የመጨረሻ ውሳኔዎችን በሰበር ማስማት ልክ ውሳኔዎች "መሠረታዊ የሕግ ስህተት " በማናቸውም ጊዜ የሚያስፈልገውን ያህል ሊሆን አይችልም የሚለውን መከራከሪያ ነጥብ ለማሳመን አዳጋች የሚሆን አይመስለኝም ። የጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ጉባኤ " መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት " በሚኖርበት ጊዜ ውሳኔውን ከመረመረ በኋላ ሳይለውጥና ሳያሻሽል እንኳ የበታች ፍርድ ቤቶች " የሕጎችን አንድ ወጥ አጠቃቀም " ለማረጋገጥ ሕጎችን እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው በመመሪያ መልክ ሊያሳስባቸውና ሊያስገነዝባቸው ይችላል ። ስለዚህ ፡ ቢያንስ ከተከራካሪዎች ወገኖች አንዱ የተሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ በጠቅላይ ፍ/ቤት በሰበር ይታይለት ዘንድ ፍላጐቱን የገለጠ እንደሆን የጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ጉባኤ ጉዳዩን ያመለክታል የሚለው ማከራከሪያ ሃሳብ ተአማኚ ይሆናል ።

ባለጉዳዮች የይግባኝ መብታቸውን ከጨረሱ በኋላ የጠቅላይ ፍ/ቤት የመጨረሻ ውሳኔዎችን በሰበር ይመለከት ዘንድ አቤቱታ ሲያቀርቡ ጉባኤው " የሕጎችን አንድ ወጥ አሠራር " የማረጋገጥ ተግባሩን ለመወጣት ሲል ጥያቄውን መቀበል ይገባዋል ። የጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ጉባኤ ሌሎች የጠቅላይ ፍ/ቤት ችሎቶችም ሆኑ ሌሎች ዝቅተኛ ፍ/ቤቶች ለወደፊቱ " መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት " ያለበት ውሳኔ እንዳይሰጡና ውሳኔያቸውንም በአግባቡ ይመረምሩ ዘንድ ለማስተማር የመጨረሻ ውሳኔዎቻቸውን መመርመር ይገባዋል ። ታዲያ የጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ጉባኤ " መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለባቸውን " የዝቅተኛ ፍ/ቤቶች ውሳኔዎችን በተመለከተ የተሻሻለውን ፍርድ ይሰጥ ወይስ ለነዚሁ ዝቅተኛ ፍ/ቤቶች የተጠቀሰው ስህተት መገኘቱን ብቻ በመመሪያ መልክ መግለጡ ያበቃዋል ?

ይህንን ጥያቄ ለመመለስ ከዚህ የሚከተለውን ጥያቄ ማንሳት አስፈላጊ ይሆናል ። ከበስተኋላው ምን ምክንያት ቢኖረው ነው ፡ ሕግ አውጭው በመንግሥት አካላት ፡ ሕዝባውያን ድርጅቶች ፡ ሸቀጦችን በማምረትና በማከፋፈል ሥራ ላይ የተሰማሩ ድርጅቶች አገልግሎት ሰጪዎችንና ግለሰቦችንም ጭምር ጥብቅ የሆነ አንድ ወጥ የሕጎችን አጠቃቀም የማረጋገጥን ተግባር ሊሰጣቸው የቻለው ? ይህንን ጥያቄ ለመመለስ የሶሻሊስት ሕብረተሰብን የሶሻያሊስት እድገት ጐዳና የሚከተሉ ሕብረተሰቦች የሚመሩበትን ጽንሰ ሃሳብና የዕድገት መመሪያዎቻውን መመርመር አስፈላጊ ይሆናል ።

የነዚህ ሕብረተሰቦች መመሪያ ሶሻሊያዝም ነው ። ፍላጐታቸው ዕድገታቸውን በሶሺያሊዝም መርሆዎች በመምራት የተፋጠነ ሕብረተሰባዊ ዕድገት ለህዝባቸው ለማምረት ነው ። እንደዚሁም ሕብረተሰባቸው የሶሻያሊስታዊ የሕብረተሰብ ዕድገት ደረጃ ላይ የደረሰላቸው ሕዝቦች ደግሞ ወደ ኮሚኒስታዊ የዕድገት ደረጃ ላይ ለመድረስ ሲሉ ዕድገታቸውን በዕቅድ በመምራት ላይ ይገኛሉ ። በአንጻሩ የሶሻሊዝምን የዕድገት ጐዳና የመረጡ በቅድመ ካፒታሊስታዊ የዕድገት ደረጃ ላይ የሚገኙ ሕዝቦች ደግሞ የደረጃ የአውሮፓ መንግሥታት የዕድገት ታሪክ እንደሚያሳየው ካፒታሊዝምን ጨምሮ ሌሎች የዕድገት ደረጃዎችን በመዝለል ሶሻሊስት

የሆነ የዕድገት ደረጃ ላይ በመድረስ ዕድገታቸውን በፕሮግራም በመምራት ሂደት ላይ ናቸው ።

በሳይንሣዊ ሶሻሊዝም መርሆዎች መሠረት ፡ ማናቸውም አመራር በሳይንሣዊ ሶሻያሊዝም መርሆዎች እስከተመራ ድረስ ሕብረተሰቦች ከፍተኛ የሆነው የሕብረተሰብ ዕድገት ደረጃ ላይ ሊደርሱ ይችላሉ ። አንድ ጊዜ እንደዚህ ዓይነት መንግሥት ከተመሠረተ በኋላ ፡ ሕብረተሰቡ የተፈለገውን የዕድገት ደረጃ በጣም አጭር በሆነ ጊዜ ይደርስ ዘንድ የያንዳንዱን የኅብረተሰብ አባል ንቃተ ህሊናና የሕብረተሰቡም የኢኮኖሚ ማኅበር በጣም አስፈላጊ ነው ። ይህንንም ግብ ለሙምታት በሶሻያሊዝም መርሆ ላይ የተመረኮዘ ሕብረተሰባዊ አውቃቀርና ፡ ግንኙነትን መፍጠር አስፈላጊ ይሆናል ። በሌላ አነጋገር ፡ የኅብረተሰቡን እርስበርስ ግንኙነትና አወቃቀር ለተተለመው የዕድገት ደረጃ እውን መሆን ይረዳሉ ተብለው የሚገኙትን ሕጐችና ደንቦች ማውጣት እጅግ አስፈላጊና የሚደነቅ ነገር ነው ። የተተለመው የዕድገት ደረጃ በሥራ ሙታየት እውን መሆን እስካለበት ድረስ ደግሞ ፡የኅብረተሰቡን የዕድገት ሁኔታ የሚጠቁሙትን እነዚህን ሕጐች ማናቸውም የሕብረተሰቡ አባል በደንብ ይጠብቃቸውና ተፈጻሚነታቸውንም ሥራዬ ብሎ መከታተል ይገባዋል ። ይህ ደግሞ በተራው ፡ ሶሻያሊስት ሕጋዊነት መረጋገጡ ግልጽ ይሆን ዘንድ የሕብረተሰቡን ግንኙነትና አወቃቀር የሚያሳዩትን ሕጐች በአውንታም ሆነ በአሉታ በሕግ ተደንግገው ጥብቅና አንድ ወጥ አጠቃቀማቸው መረጋገጡ እጅግ አስፈላጊ መሆኑን ያሳያል ። ካፒታሊስታዊ የዕድገት ጐዳና የሚከተሉ ኅብረተሰቦች የሕግ ሥርዓት ውስጥ ምናልባትም “ ሊደፈሩ ” (ሊሰኩ) የማይችሉትን ሕጋዊ ያልሆኑ የፍርድ ቤቶች የመጨረሻ ውሳኔዎች የሶሻያሊስት ዕድገት ጐዳና በሚከተሉ አገሮች ግን የመንግሥት ባለሥልጣናት ጣልቃ በመግባት ጠፍትሄ ይሰጧቸው ዘንድ የሚያስችላቸው መሣሪያዎች ማዋቀር እጅግ አስፈላጊ ይሆናል ። ሕግ በማንኛውም ሕብረተሰባዊ ዕድገት ጐዳና ለማደግ በሚፈልጉ አገሮች ውስጥ አንዳንድ ጠቃሚ መሣሪያ መቆጠሩን ሕግ በሶቪዬት ኅብረት ውስጥ ከሚጫወተው ሚና አንጻር ልንመለከተው እንችላለን ። ይህም ችግር ለማቃለል የሚረዳ የሕግ ተግባር ተብሎ የተቀመጠው ሲሆንና ፡ በዚህም ሕግ ትምህርት ሰጪነት ሚና ከመጫወቱም በላይ ሰዎች የኅብረተሰቡን ሕጋጋት እንዲማሩና የሚጠበቅባቸውንም በኅብረተሰቡ ውስጥ ሊያደርጉትና ሊከተሉት የሚገባቸውን ግንኙነት እንዲያውቁት በማድረግ ለተሰማለት [14] የሕብረተሰብ ዕድገት ደረጃ የሚደነቅ አስተዋጽኦ ድርሻውን ይከፍላል ። ሕግ ከዚህ በላይ የጠቀስነውን በተግባር እንዲፈጸም አስፈላጊ ከሆነ ጥብቅና አንድ ወጥ አጠቃቀሙን የሚያረጋግጡ መሣሪያዎች ደግሞ በአንጻሩ መዋቀር አለባቸው ።

ከላይ ለማስገንዘብ እንደሞከርነው ፡ የነዚህ መሣሪያዎች በተግባር ላይ መዋል ለግለሰቦች የተተወ እንደሆነ ደግሞ የሕጐችን ጥብቅ አሠራር ማረጋገጥ ስለማይችሉ የሕጐች ጥብቅና አንድ ወጥ አጠቃቀም ሊኖር አይችልም ። ለዚህም ማስረጃ የሚሆነን ወንጀሎችን በነስ አቤቱታ አቅራቢነት ብቻ የሚያስቀጣ ወንጀል ቀላልና (የግል አቤቱታ) ከባድ ወንጀሎች በማለት መከፈል ነው ። ቀላል ወንጀሎች የግለሰቦችን ግላዊ ጥቅም ብቻ ሊነኩ የሚችሉ ወንጀሎች ናቸው ። ይህ ከሆነ ዘንዳ በነስ አቤቱታ ብቻ የሚያስቀጣ ወንጀል ወደ ህግ ፊት ማቅረቡና ተገቢውን ቅጣት ማስወሰን ጉዳቱ በደረሰበት ግለሰብ ፈቃድ ላይ ብቻ የተመሠረተ ይሆናል ። በሌላ ወገን ደግሞ ከባድ ወንጀሎች የሚመለከቱት የጉዳቱ ቀጥተኛና ቀዳሚ ተጐጂውን ግለሰብ ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ ህብረተሰቡን በመሆኑ ወደ ህግ ፊት ማቅረቡና ተገቢውን ቅጣት የማስቀጣቱ ኃላፊነት ለመንግሥት አካል ይሰጣል ።

ይህም የመንግሥት አካል የጠቅላይ ዐቃቤ ህግ መሥሪያ ቤት ነው ። ይህም ለአንድ ማህበረሰብ እድገት እጅግ አስፈላጊና ያለሱም ዕውን ሊሆን የማይችለውን የሕግንና ሥርዓትን መከበርና መጠበቅ ለማረጋገጥ ህብረተሰቡ የወንጀሎችን መፈጸም መከላከል ስለሚገባው ነው ። ነገር ግን ህብረተሰቡ ወንጀሎችን ለመከላከል ብርቱ ጥረት እያደረገ እያለ ወንጀሎች ተፈጽመው ሲገኙ ከባድ ወንጀል ፈጽመው የተገኙ ግለሰቦች በሙሉ ህብረተሰቡ ተገቢውን ቅጣታቸውን በመስጠት ደግመው ጥፋት ላይ እንዳይገኙ ማድረግ ይኖርበታል ። ከባድ ወንጀል የፈጸሙ ግለሰቦችን የመቅጣት ኃላፊነት የተፈጸመው ወንጀል በመጀመሪያ ደረጃ ጉዳት ለደረሰባቸው ግለሰቦች መተው ህብረተሰቡ ለወደፊት ወንጀል ሊፈጽሙ ይችላሉ ተብለው የሚጠረጠሩትን ግለሰቦች በሙሉ ከዚህ አድራጐት ይገቱ ዘንድና ወንጀልንም ሳይፈጽም አስቀድሞ ሊደረግ የሚገባውን ዋና የህብረተሰቡን ፍላጐትና መልካም አስተሳሰብ ፋይዳ ቢስ ማድረግ ይሆናል ። ይህ ደግሞ ጉዳት የደረሰባቸውን ግለሰቦች ወንጀለኞችን ለተለያየ ምክንያቶች ለምሳሌም እንደ ካሳ የመሳሰሉትን ካገኙ በኋላ ወንጀለኞቹ ተገቢውን ቅጣት ሲያገኙ ነጻ እንዲለቀቁ የተመቻቸ ሁኔታዎችን እንዲፈጥሩ ያበረታታቸዋል ።

የአንድ አገር የሕግ ሥርዓት ለአገሪቱ ማህበራዊ ዕድገት አስፈላጊ መሆኑን ከተገነዘብን ዘንዳ በተለይም የሶሻያሌስት የዕድገት ጉዳናን የሚከተሉ ህዝቦች ለሚያስሙት የዕድገት ደረጃ የሚከተሉት የሕግ ሥርዓት ከፍተኛ አስተያየት ያደርግ ዘንድ የመጨረሻው ውሳኔዎችን በሰበር መስማት የመሳሰሉትን መሣሪያዎች በመንግሥት ባለሥልጣኖች ኃላፊነት ሥር ማዋቀር ይገባቸዋል ። በሰበር ሰሚነት መሠረታዊ የሆኑ የሕግ ስህተቶች ሊታረሙ እስከቻሉ ድረስ የሕጐች ጥብቅና አንድ ወጥ አጠቃቀም መረጋገጡ አከራካሪ አይሆንም ።

የሆነው ሆኖ ግን በተመሳሳይ ምክንያት እንደሚታወቀው ሁሉ " መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት የመጨረሻ ውሳኔ በስውር ቢሻሻልም ጥቅም ሊያገኝ የሚችለው ወገን የአፈጻጸሙን ሁኔታ ተከታትሎ የመጨረሻ ውጤት ለማግኘት ጥረት እስካላሳየ ድረስ የመጨረሻ ውሳኔ ተሻሻለ ወይም ተለወጠ ለማለት አያስደፍርም ። ነገር ግን ፍርዶች ሳይፈጸሙ መቅረታቸው ሊሻሻሉ ወይም ሊቀየሩ አይገባቸውም ማለት አይደለም ። ምክንያቱም " መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት" የመጨረሻ ውሳኔዎች መርምሮ ፍርዱን መቀየር ወይም ማሻሻል ከላይ የጠቀስነውን " የሕግን መልካም አስተዳደር ለማረጋገጥ ይቻል ዘንድ አንድ ወጥ የሕግ አጠቃቀም " ለፍርድ ቤቶች ፍትህ የተመላበት አሠራር አስፈላጊ መሆኑን ማረጋገጥ ከመሆኑም በላይ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉባኤ አብይ ተግባር ሆኖ ይገኛል ።

የሆነው ሆኖ ግን የሕጐችን አንድ ወጥ አጠቃቀምን ለማረጋገጥ የበታች ፍርድ ቤቶችን ውሳኔዎች መመርመር ያስፈልጋል የሚለው የመከራከሪያ ነጥብ ውሳኔዎቹ " መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት " እንዳለባቸው ተቆጥሮ ሊመረምሩ ያስፈልጋል የሚለውን አቋም ሊያሰይዘን አይገባም ።

ከላይ እንደጠቀስነው የጠቅላይ ፍ/ቤት ጉባኤ የበታች ፍርድ ቤቶች እንዴት አድርገው ሕጐችን በሥራ ላይ ማዋል እንዳለባቸው መመሪያዎችን መስጠት ይችላል ወይ የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል ። በዚህም አንድ ባለጉዳይ በተሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ ላይ ቅሬታውን ማሰማትና ውሳኔውም ይመረመርለት ዘንድ ጥያቄ የሚያቀርብ ከሆነ በመጨረሻ ላይ የተለወጠለትን ወይም የተሻሻለበትን ውሳኔ ለማስፈጸም የሚጠይቅ መሆኑን መቀበል እጅግ አስፈላጊ ይሆናል ። ይህም ሊሆን የሚችለው ሙቼውንም ቢሆን ውሳኔው እንዲሻሻልለት ጥያቄ

ውን ያቀረበው ሰው በሰበረ ሰሚው ጉባኤ የተሰጠው ወይም የተሻሻለበት ውሳኔ የበለጠ የሚጠቅመው ሆኖ የተገኘ እንደሆነ አያጠራጥርም የጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ጉባኤም ቢሆን ከአንድ ከዝቅተኛ ፍ/ቤት በተለይ ውሳኔ ላይ ተበደልኩ ባይ ባለጉዳይ የሚጠብቀው ይኸንኑ ከላይ የጠቀስነውን ቅድመ ሁኔታ ብቻ ነው ። ይህ ደግሞ እንደገና አንድ ተበደልኩ ባይ ባለጉዳይ ጥያቄ ቢያቀርብም ባያቀርብም የጠቅላይ ፍርድ ቤት ከተግባሮቹ አንዱ የሆነውን ማለትም ፦

የዳኝነት አሠራርን ለማሻሻልና የሕጎችን አንድ ወጥ አፈጻጸም በማረጋገጥ ለፍርድ ቤቶች መመሪያዎችን መስጠት [15]

ለመወጣት ሲል ብቻ የዝቅተኛ ፍ/ቤቶችን የመጨረሻ ውሳኔዎች መመርመሩ ተቀባይነት ያለው አሠራር ነው ።

ፍርድ ቤቶች ፍትህ ነክ ተግባራቸውን ለመወጣት አንድ ወጥ የሕጎችን አጠቃቀም ይከተሉ ዘንድ ማረጋገጥ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ኃላፊነት ሆኖ ሳለ ከዚህ ቀጥሎ ለተመለከተው አንዱ የጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ተግባር ምን ትርጉም መስጠት ይገባናል የሚለውን ጥያቄ ማንሳት እጅግ አስፈላጊ ይሆናል ። ይኸውም ፦

የፍርድ ቤቶችን ውሳኔዎችና ትዕዛዛት ሕጋዊነት መከታተል ። [16]

ለዚህ ጥያቄ መልስ ከመስጠታችን በፊት የሚከተሉትን ነጥቦች ከሃሳባችን ውስጥ ማስቀመጥ ይኖርብናል ። ከላይ እንደጠቀስነው ፡ ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ የሕጎችን ትክክለኛና አንድ ወጥ አጠቃቀም የሚያረጋግጥበት መሳሪያ ከነጥቦቹ መካከል አንዱ ነው ። ይህም ከሕግ ውጭ የተሰጡ የዝቅተኛ ፍርድ ቤቶችን ውሳኔዎች በሥልጣን የሆኑ ፍርድ ቤቶች እንዲሠርዙዋቸው ለማሳሰብና ለማመልከት ጭምር ነው ። ስለሆነም ጠቅላላው በሥልጣን ከፍተኛ የሆኑ ፍርድ ቤቶች በተለይም የጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰበር ሰሚ ጉባኤ ከሕጉ ውጭ የሆኑ የአነስተኛ (ዝቅተኛ) ፍርድ ቤቶችን ውሳኔዎች በመሻርና በመለወጥ ሶሻያሊስት ሕጋዊነትን ማረጋገጣቸው ግልጽ ይሆናል ።

ከላይ እንደተጠቀሰው በአዕምሮአችን ልናስታውሰው የሚገባን ሁለተኛ ነጥብ ቢኖር በሶሻሊስት ፍልስፍና የሚመሩና የሶሺያሊስት የዕድገት ጎዳና የሚከተሉ ሕብረት ሰቦች የሕግ ሥርዓት ፡ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉባኤ " ቀሲቃሽ " ለአሠራሩም ከተከራካሪ ወገኖች በአንዱ አማካይነት " ጉትጐታና ቅስቀሳ የሚያስፈልገው " ከሆነ ይህንኑ ሥርዓት በሥራ ለመተርጐም ሕግ በሶሺያሊስት ሥርዓት ማህበር ውስጥ ሊጫወተው የሚገባውን ሚና የበለጠ ማጕልበት የጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉባኤ የሶሻያሊስት ህጋዊነትን የማረጋገጥ ድርሻውን መወጣት መቻሉን ይጠይቃል ። ታዲያ ይህ መሆን ካለበት ደግሞ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉባኤ በፍ/ቤቶች ውሳኔዎች ላይ ከተከራካሪ ወገኖች ምንም ዓይነት አቤቱታ ባይሰነዘርም እንኳን ፡ ተገቢውን መመሪያ ለዝቅተኛ ፍርድ ቤቶች መስጠት ይቻለው ዘንድ የበታች ፍርድ ቤቶችን ውሳኔዎች ሊመረምር ይገባዋል ።

ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተገቢ የሆኑ መመሪያዎች መስጠት ይችል ዘንድ በአንድ ወጥ የህግ አጠቃቀም ላይ ያልተመረኮዙ ውሳኔዎች በሚኖሩበት ጊዜ ይህንኑ ሁኔታ ለጠቅላይ ፍርድ ቤቱ የማሳወቅ ኃላፊነት በጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ላይ የተጣለ መሆኑ ግልጽ ነው ። ይህ ተግባር የፍ/ቤቶችን የመጨረሻ ውሳኔዎችንም መጨመሩ ደግሞ በእኳያው ግልጽ ነው ። በወንጀል ነክ ጉዳዮች ላይ ብቻ አግባብ ካለው ከጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ጋር ሲነጻጸር የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚ

ዳንት ” መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ” ያለባቸውንና ሊሻሻሉ የሚገባቸውን ውሳኔዎች ለጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉባኤ ማቅረብ የሚችል ዓይነተኛ የመንግሥት ባለሥልጣን ነው ። ይህ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ተግባር የጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉባኤ አንድ ወጥ የሕግ አጠቃቀም የማረጋገጥ ተግባሩን እንዲወጣ የሚያደርገው ቅድመ ሁኔታ መፍጠሩን ስንመለከት ከላይ የጠቀስነው ሁኔታ እውነታነቱ የበለጠ ግልጽ ይሆናል ።

በሌላ ወገን ደግሞ ፣ የጠቅላይ ዐቃቤ ህግ መሥሪያ ቤት ፍርድ ቤቶች ፍትሐብሔር ጉዳዮችን በተመለከተ የመጨረሻ ውሳኔ ለመስጠት ይቻላቸው ዘንድ በፍርድ ቤቶች የተሰጡ ውሳኔዎችንና ትዕዛዛትን ይጠቅሙ አይጠቀሙ የሚያውቅበት ምንም መንገድ የለውም ። በተጨማሪ ፣ ከላይ ለማስቀመጥ እንደተሞከረው የጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰበር ስሚ ጉባኤ ጠቅላይ ፍርድ ቤትን ጨምሮ በበታች ፍርድ ቤቶች ተግባራቸውን ሲያከናውኑ የሚሰጡትን ትዕዛዛትንና ውሳኔዎችን በመመርመር አንድ ወጥ የሕግ አጠቃቀም መኖሩን ማረጋገጥ ፣ አለበት ። የውሳኔዎችንና የትዕዛዛትን ሕጋዊነት የመከታተል ተግባርና “ ኃላፊነት ” የሕግን መልካም አስተዳደር ማሻሻልና የሕጎችን አንድ ወጥ አጠቃቀም “ ማረጋገጥ ” በሚለው ጽንሰ ሀሳብ ውስጥ የሚያጠቃልል መሆኑን ስናስተውል ይኸው ተግባር ለጠቅላይ ፍርድ ቤት ሊተው ይገባል ። የጠቅላይ ዐቃቤ ህግ መሥሪያ ቤት ሊያደርግ የሚችለው ነገር ቢኖር ለሌሎች የበላይ ፍርድ ቤቶች ዳኞች ይግባኝ ማሰማት ብቻ መሆኑን ስንመለከት ከዚህ በላይ የገለጽነው ጉዳይ ከምንጊዜም ውም የበለጠ ምክንያታዊ ይሆናል ።

## የግርጌ ማስታወሻዎች

* የኢ. ሀ. ድ. ራ. ምክትል ዐቃቤ ህግ ኤል ኤል ቢ ፡ የሕግ ፋኩልቲ ፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ / ቀ.ኃ.ሥ.ዩ./ ፤ የፒ. ኤች. ዲ. እጩ ፡ ኤድንበርድ ክርድልጅ ዩኒቨርሲቲ/ዩጐስላቪያ/ በአሁኑ ጊዜ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፡ የሕግ ፋኩልቲ ፡ የገሚስ ጊዜ መምህር ።

1. የጠቅላይ ፍርድ ቤት መቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 9 ፡ አንቀጽ 4/4 በግልጽ ተለይቶ እስካልተሰጠ ድረስ በዚህ ቁጥር የተመለከቱ አዋጆች በሙሉ እ. አ. በ1987 የታወጁ ናቸው ።/

2. በፍርድ ቤቶች አደረጃጀት ውስጥ በማንኛውም ከፍታ የሚገኝ ፍርድ ቤት ክፍል የሚያመለክት የአማርኛ ቃል ። ነገር ግን እዚህ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉባኤ ለማለት ተጠቅመንበታል ።

3. የዚሁ አዋጅ አንቀጽ 20

4. የዚሁ አዋጅ አንቀጽ 5/ 1/

5. የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ መሥሪያ ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ይመልከቱ ።

6. የዚሁ አዋጅ አንቀጽ 10

7. ከላይ በቁጥር 1 የተመለከተውን አዋጅ አንቀጽ 5/ 2/

8. ከላይ በቁጥር 5 የተመለከተውን አዋጅ አንቀጽ 4

9. —”— —”— —”— —”— —”— አንቀጽ 10//1/

10. ከላይ በቁጥር 1 የተመለከተውን አዋጅ አንቀጽ 3

11. —”— —”— —”— —”— —”— አንቀጽ 22/2/

12. ሶሻያሊስት ሕጋዊነትን የማረጋገጥ ተግባራቸውን የመቆጣጠሩ ሥልጣን ከጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ሥልጣንና ተግባር ውጭ የሆኑ መንግሥታዊ አካላት መኖራቸው የታወቀ ነው መንግሥት ምክር ቤት አንዱ ነው ።

13. ከላይ በቁጥር 3 ላይ ይመልከቱ

14. በመፍትሔ ሰጭነት የሕግ ተግባራት ላይ ለተደረገው ውይይት ፡ ጀምስ ፡ ኤል ሄልደብራንድ ፡ ዘ. ሶሲዮሎጂ ኦፍ ሶቪየት ሎው /ኒው ዮርክ ፡ 1972/ ፡ 111 ይመልከቱ ።

15. ስለ ሶቪዬት ኅብረት ጠቅላይ ፍርድ ቤት የዚሁ ዓይነት ተግባር ፡ ገጽ ፤ ኤ ፡ ትሩብኒኮቭ ፡ “ ሪቪው ኦፍ ዲስገርንስ ስሩ ጁዲሺያል ሱፐርቪዢን” ፡ ሶቪዬት ሎው ኤንድ ገቨርንሜንት /ቅጽ 9 ፡ ቁጥር 2/፡ገጽ 188—204ና ቢ. ኩሊኖብ ፡ “ ዘ ሱፕሪም ኮርት ኦፍ ዩ ኤስ ኤስ አር—ዘ ሃያስት ሊንክ ኢን ዘ ሶቪዬት ጁዲሺያል ሲስተም ” ሶቬዬት ሎው ኤንድ ገቨርንሜንት /ቅጽ 17 ፡ ቁጥር 2/ ገጽ 57—74

16. ከላይ በቁጥር 3 የተጠቀሰውን አዋጅ አንቀጽ 13 ይመልከቱ ።